# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 296 ጥር 2 2006 ገጽ 1


አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ግንቦት ሰባት የፍትህ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ እነዚህ ዜጎች በህወሃት ተግድለው እንደተጣሉ ያምናል። ውሎ አድሮ እውነቱ እስከሚወጣ ድረስ ግን ዜጎች በሙሉ ይሄን ግድ በተመለከተ መረጃ የመሰብሰብና የማሰረጫት ሥራችውን አጠናክረው እንዲቀጥሉ እናሳስባለን። ይሄን ወንጀል የፈፀሙ አካላት መጠየቅ አለባቸው። የዜጎች ደም እንዲሁ በከንቱ ፈሶ መቅረት የለበትም።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የግንቦት ሰባት ከወያኔ ዉጭ ዜጎችን በጅላ በመገደል የሚጠረጠር ሌላ ኃይል የለም አለ

ባሳለፍነው ሳምንት አዲስ አበባ ውስጥ ፈረንሳይ ለጋሲዎን አካባቢ በሚገኘው የክቡርዘበኛ የጦር ካምፕ በጅምላ የተቀበሩ 6 አስከሬኖች መገኘታቸውን ተከትሎ የግንቦት ሰባት የፍትህ የነጻነት እና የዴሞክራሲ ንቅናቄ እነዚህ ዜጎች በህውሀት መራሹ የወያኔ አገዛዝ ተገድለው እንደተጣሉ እንደሚያምን ገልጿል።አንድ አይነት ቀለም ባላቸው ብርድ ልብሶች ተጠቅልለው ከተገኙት ስድስት አስከሬኖች መካከል የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ ታስረውበት የነበረው ሰንሰለት እንኳ እንዳልወለቀ እና ከተቀሩት አንዱ ደግሞ ሁለት እጆቹ የፊጥኝ ታስረው መገኘቱ ግድያው በክርብ እንደተፈጸመ አንዱ አስረጅ ነው በማለትም አስታውቋል።እንዲህ በጭካኔ የተገደሉ ዜጎችን በማስመልከት በመንግስት ተብየው አካል አለመገለፁ እና ግቢውን በማስተዳደር ላይ የሚገኘው የሶስተኛው ክፍለ ጦርም የጉዳዩ ተባባሪ መሆን የበለጠ አሳዛኝ እንደሆነም አስታውቋል። የግንቦት ሰባት የፍትህ የነጻነት እና የዴሞክራሲ ንቅናቄ እንዳስታወቀው ይህንን ጉዳይ ህብረተሰቡ፣ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች እና የፖለቲካ ፓርቲዎች የበለጠ ማጣራት ሃላፊነት እንዳለባቸው እና የወያኔን አገዛዝ ለተጠያቂነት ማቅረብ እንዳለባቸው አስታውቋል።

## ወያኔ የአገሪቱ ባለስልጣኖች ለኢሳት ቴሌቪዥንና ሬድዮ ቃለምልልስ እንዳይሰጡ አዘዘ

ኢትዮጵያ ዉስጥ ዜጎች የሚናገሩትን፤ የሚጽፉትን፤ የሚያነቡትንና የሚሰሙትን ብቻ ሳይሆን የሚተነፍሱትን አየር ጭምር መቆጣጠር የሚፈልገዉ ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ ማንኛዉም የመንግስት ባለስልጣን፤የገዢዉ ፓርቲ አባላትና ተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች ለኢሳት ቴሌቪዥንና ሬድዮ ቃለ መጠይቅ እንዳይሰጡ አዘዘ። ባለስልጣናቱ ይህንን ማስጠንቀቂያ ተላልፈዉ ምንም አይነት ቃለምልልስ ለኢሳት ቢሰጡ በአሸባሪነት እንደሚከሰሱ ይኼዉ የወያኔ ማስጠንቂያ አስምሮበት አልፏል ። ከዚህ በተጨማሪ ይህ ማስጠንቀቀያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለኢሳት መረጃ መስጠትና አለምስጠት የመንግስት ባለስልጣናት ከሚገመገሙብት መንገድ አንደኛዉና ዋነኛዉ መመዘኛ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል;፡ ይህ ማስጠንቀቅያ የተጻፈበት መመሪያ ለህዝብ ግንኙነት ሰራተኞች፣ ለደህንነት ሰራተኞች፣ ለመንግስት ባለስልጣናት ና ለኮሚኒኬሽን ባለሙያዎች መተላለፉ ታውቋል።

መመሪያውን ያወጣዉ የብሄራዊ መረጃ ደህንነትና ኮሚኬሽን መስሪያ ቤት የመንግስት ባለስልጣናት ለኢሳት መረጃ በመስጠት ኢሳትን ህጋዊነት እያላበሱትና ሌሎችም ዜጎች አንዲናገሩበት እያደፋፈሩ ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## ሰማያዊ ፓርቲ ሀሳቤን ለመግለጽ የማንም ፈቃድ አያስፈልገኝም አለ

በቅርቡ ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ ለኢሳት ሬድዮና ቴሌቪዥን ቃለመጠይቅ መስጠት በህግ ያስጠይቃል ሲል የሰጠዉን የማንአለብኝነት ማስጠቀቂያ አስመልክቶ በቅርቡ ሰማያዊ ፓርቲ በሰጠዉ መግለጫ ፓርቲዉ ቃለመጠይቅ ለመስጠትም ሆነ ሀሳቡን ለመግለጽ ማንንም እንደማይጠይቅ ተናገረ። ሀሳባችንን ባሰኘን መንገድ መግለጽም ሆነ የሌሎችን ሀሳብ መስማት ህገ መንግስቱ ያጎናጸፈን መብት ነዉና ማንም ሊወስድብን አይገባም የሚለዉ ሰማያዊ ፓርቲ የምንናገርበትን የመገናኛ ብዙሃን ማንም እንዲመርጥልን ወይም እንዲወስንልን አንፈቅድም ብሏል። እንደ ሰማያዊ ፓርቲ ቃል አቀባኢ አባባል በኢሳትም ሆነ እድሉ አይሰጠዉም እንጂ ቢሰጠዉ ፓርቲዉ በኢቲቪም ወይም በሌሎችም የመገነኛ አዉታሮች አቋሙንና እምነቱን ማስተላለፍ አሁንም ሆነ ለወደፊት ይቀጥላል። ሰማያዊ ፓርቲ ታህሳስ 25 ቀን 2006 ዓም በኢቲቪ የተላላፈውን ዶክመንታሪ ፊልም "የእብሪት መልዕክት" ያዘለና እና "ከተራ ርካሽ ፕሮፓጋንዳነት የማያልፍ የሕግና የዲሞክራሲያዊ መብት ገደብን ካለማወቅ የሚመነጭ አስተሳሰብ ነው" ሲል አጣጥሎታል።

ኢትዮጵያ ዉስጥ መገደብ ካለበት ከሚሰራቸዉ አስጸያፊ፤ ጸረ ህዝብና ህገወጥ ስራዎች መታቀብ ያለበት የወያኔ አገዛዝ እንጂ ህግ መንግቱን አክብረዉ የሚንቀሳቀሱ ፓርቲዎችን ግለሰቦች አይደሉም የሚሉ ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

ግዜ

## የቻይና ኤክስፖርት ባንክና ኤክስፖርት ክሬዲት ኢንሹራንስ ኮርፖሬሽን በወያኔ ላይ ማማረራቸዉ ተሰማ

ታዋቂዎቹ የቻይና መንግሥት የፋይናንስ ኩባንያዎች ቤጂንግ ለሚገኘው የወያኔ ኤምባሲና በግልባጭ ደግሞ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተብዬው መስርያቤት በጋራ በጻፉት ደብዳቤ፣ የወያኔ መንግሥት የግዥ ሒደት ግልጽነትና ተጠያቂነት የጎደለውና አዳዲስ የቻይና ኩባንያዎች ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገቡ በር የዘጋ ነው በማለት ቅሬታቸውን አሰምተዋል። የፋይናንስ ተቋማቱ እንደሚሉት፣ ቀደም ብለው የገቡ ጥቂት የቻይና ኩባንያዎች ግልጽ ባልሆነ መንገድ ሥራዎችን እያገኙ እንደሆነና በርካታ ትልልቅ ኩባንያዎች ግልጽ የግዥ ሒደት ባለመኖሩ ወደ ኢትዮጵያ በመግባት ተወዳድረው ለመስራት መቸገራቸውን ገልጸው፣ ጉዳዩ መስተካከል እንዳለበት በአፅንኦት አሳስበዋል። ይህ በንዲህ እንዳለ የቻይና መንግሥት ጉዳዩ እጅግ እንዳሳሰበው የታወቀ ሲሆን ባለሥልጣናትን ያሳሰበው ጉዳይ በተለይ በኢነርጂ፣ በትራንስሚሽን፣ በሰብ ስቴሽን፣ በመስኖ፣ በመጠጥ ውኃ ዘርፎች አዳዲስ የቻይና ኩባንያዎች ለመግባት ፍላጎት ቢያሳዩም በተለያዩ አሻጥሮች እና ማነቆዎች ሳቢያ ለመግባት አለመቻላቸው እንደሆነ ታውቋል።

ቀደም ሲል የገቡ የቻይና ኩባንያዎች ከተወሰኑ የጉጅሌው ባለሥልጣናትና ከቻይና ኤምባሲ ኃላፊዎች ጋር በመመሳጠር ሥራ እንዳያገኙ እየተደረገ መሆኑን በመጥቀስ፣ ለወያኔው አገዛዝ አቤቱታ ማቅረባቸው መዘገቡ ይታወሳል። ነገር ግን ጉዳዩ ባስቸኳይ ባለመታረሙና ችግሩም አሳሳቢ በመሆኑ ሁለቱ የቻይና የፋይናንስ ተቋማት ለወያኔው ጉጅሌ አገዛዝ ቅሬታቸውን ከገለጹት ከሌሎች 18 የቻይና ኩባንያዎች ጎን በመቆም አቤቱታቸውን በድጋሚ አቅርበዋል።

( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## አክራሪዎቹ የህወሃት አባላት የመከላከያ አዛዥነቱ ከህወሀት እጅ እንዳይወጣ እየጣሩ ነዉ

ስልጣን የኛ ብቻ ነዉ ብለዉ የሚያምኑት ዘረኞቹ የወያኔ መሪዎች የአገር መከላከያ ዋና አዛዥነቱ ቦታ ከትግርኛ ተናጋሪዎች እጅ እንዳይወጣ ከፍተኛ ጥረት እያደረጉ መሆኑን በመከላከያ ውስጥ ከሚገኙ ወታደራዊ አዛዦች የተገኘዉ መረጃ አመለከተ። አክራሪና ዘረኛ የሆኑት የህወሃት ባለስልጣናት ጄኔራል ሳሞራ የኑስን ለመተካት ከሁሉም በላይ የተሻለ ቦታ ላይ የነበሩትን ጄ/ል አበባው ታደሰን ሰበብ አስባብ በመፈለግ አድማ ለማድረግ አስበዋል ብለዉ ሃላፊነታቸዉ እንዲቀነስና ጄኔራሉ ከውድድር ውጭ እንዲሆኑ ማድረጋቸዉን የመከላከያ ምንጮቻችን ገልጸዋል። ይህንን የህወሀቶችን አድማ በማስተባብና በመምራት ጄኔራል ሞላ ሀይለማርያምና ጄኔራል ሰአረ መኮንን ዋና ዋናዎቹ መሆናቸዉ ታዉቋል። ገብረመስቀል ቀዳሚዉ እንደሆነ ወታደራዊ ምንጮቻችን ገልጸዋል።

## ፋሽስት ወያኔ ለመጪው ዓመት ምርጫ ከወዲሁ ቅስቀሳ መጀመሩ ታወቀ

ህግን የተከተለ ምንም አይነት የፖለቲካ ሰርአትና ሁሉንም ወገኖች በእኩልነት የሚያስተናግድ የምርጫ አካል በሌለባት ኢትዮጵያ ዉስጥ ወያኔ የተለመደ የምርጫ ድራማዉን ሊያሳየን ቅስቀሳ መጀመሩን ከወደ አዲስ አበባ የሚደርሱን ዜናዎች አስረዱ። የፖለቲካ ፓርቲዎችን አጥፍቶ፤የሚናገሩ አፎችን ዘግቶና የሚጽፉ እጆችን አስሮ የሀገሪቱን የፖለቲካ መድረክ ብቻዉን የሚፈነጭበት ወየኔ ከማን ጋር እንደሚወዳደር ባይታወቅም የምርጫ ሽርጉዱን ግን ካሁኑ መጀመሩን በሚቆጣጠራቸዉ የዜና ማሰራጫ አዉታሮቹ በኩል አሰምቷል። ተቃዋሚ ድርጅቶች በምንም አይነት ከሕዝብ ጋር እንዳይገናኙ እንቅፋቶችን በመፍጠርና በቀጥታም ጦሩን በመላክ ሲከለክል የከረመው ፋሽስት ወያኔ መልካም አስተዳደርን ለማሻሻል፣ ሙስናን ለመቀነስ እንዲሁም ልማትን ለማፋጠን በሚል ሰበብ የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎችን በማደራጀትና በሚፈልገው መልኩ በማሰልጠን ለሚቀጥለው ዓመት ምርጫ ቅስቀሳ መጀመሩ ታወቀ።

ፋሽስት ወያኔ ከዚህ ቀደም ሲያደርግ እንደነበረው ለመጪው ምርጫ ዝግጅት ይረዳው ዘንድ ለማትና መልካም አስተዳደርን ለማፋጠን በሚል ርእስ የወረዳ፣ የክፍለከተማና የከተማ የሕዝብ አማካሪ ምክር ቤቶችን እንዲሁም የአነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት፣ የሴቶችና ወጣቶች ፎረሞች አባላትን ከሕዝብ ሃብት በመዝረፍና በጀት በመመደብ ለራሱ ጎጠኛ ፓርቲ የምርጫ ቅስቀሳ ስልጠና በማዋል ላይ ነው።

ገና ከሕዝብ ጋር ይገናኙብኛል ብሎ በመስጋት የተቃዋሚ ፓርቲዎችን እንቅስቃሴ ከወዲሁ እየገደበ ነው የሚሉ ወገኖች "ፋሽስት ወያኔ ራሱ እስካደረገው ድረስ ሁሉም ነገር ትክክል ነው። ከግብር የተሰበሰበ የሕዝብ ሃብት፣ በድሃው ሕዝባችን ስም የተገኘ የርዳታ ሃብትና ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

# የቀደምቶቹን ወንጀል ለማጋለጥ መቃብር ሲምስ የኖረው ወያኔ በራሱ ጦር ካምፕ ውስጥ የተገኘውን አስከሬን መደበቅ ለምን አሰፈለገው?

አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ፈረንሳይ ለጋሲዮን በሚገኘው የክብርዘበኛ ጦር ካምፕ ውስጥ ማንነታቸው ያልታወቁ የ6 ዜጎች አስከሬን ለመንገድ ሥራ በተሠማሩ ቆፋሪዎች አማካኝነት መገኘቱ የሰሞኑ አሳዛኝ ዜና ነው።

አንድ አይነት ቀለም ባላቸው ብርድ ልብሶች ተጠቅልለው ከተገኙ 6 አስከሬኖች የመጀመሪያዎቹ ሁለት ሰለባዎች ታስረውበት የነበረው የእጅ ሰንሰለታቸው እንኳ እንዳልወለቀና ከተቀሩት የአንዱ እጆች ደግሞ የፍጥኝ ወደ ኋላ እንደታሰሩ መገኘታቸው ግድያው በቅርብ እንደተፈፀም አንዱ አስረጂ ነው።

በእንዲህ አይነት ጭካኔ የተገደሉ ዜጎች አስከሬን መገኘት በመንግሥት ተብየው አካል ካለመገለጹም በላይ ግቢውን በማስተዳደር ላይ የሚገኘው 3ኛ ክፈለ ጦርም ሆነ በግብር ከፋይ ገንዘብ የሚተዳደሩ መገናኛ ብዙሃን እስከዛሬ አንድም ቃል መተንፈስ አለመፈለጋቸው ጉዳዩን እጅግ የሚያሳዝን ብቻ ሳይሆን የሚያስገርምም አድርጎታል። ይባስ ተብሎም በመንገድ ሥራ ቁፋሮው የበለጠ አስከሬን ሊወጣ ይችላል በሚል ስጋት አካባቢው በፖሊስ እንዲታጠር ከተደረገ በኋላ ሥራውም እንዲቋረጥ ተደርጓል።

በፓለቲካ መስመር ልዩነት ምክንያት ደርግ ያለ ርህራሄ የጨፈጨፋቸውን ከመቃብር እያወጣ ዘመድ አዝማድ በማላቀስ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት ሲዳክር የኖረ አገዛዝ በእንዲህ አይነት አሳዛኝ ሁኔታና አጋጣሚ የተገኘውን የጅምላ አስከሬን አይቶ እንዳላየ ለማለፍ መሞከሩ ለምን ይሆን?

አብዛኛው የአዲስ አበባ ነዋሪ እንደሚያስታውሰው የክብር ዘበኛ ጦር ካምፕ በመባል የሚታወቀው የጃን ሜዳ 3ኛ ክፍለ ጦር ግቢ ድህረ ምርጫ 97 ወያኔ ለጅምላ እስር ቤትነት ከተጠቀመባቸው የማጎሪያ ቦታዎች አንዱ ነበር። ከዚያን ጊዜ በፊትና በኋላም ቢሆን ካምፑ በወያኔ ጠላትነት ተፈረጀ በጸጥታ ሠራተኞች ከታገቱ በኋላ አድራሻቸው እስከዛሬ ተሰውሮ ላሉ በርካቶች በምስጢር እስርቤትነት በማገልገል ላይ ከሚገኙ ወታደራዊ ካምፖች አንዱ እንደሆ ይታወቃል።

ዘመድ አዝማዶቻቸው ይመለሳሉ ብለው ሲጠብቋቸው ሳይመለሱ እንደወጡ የሚቀሩ በርካታ ዜጎች አሉ። በእንዲህ ሁኔታ ወጥተው ከቀሩ መካከል ከሰሞኑ የስድስቱ መቃብር በአጋጣሚ ተገኝቷል። የተገነዙበት ብርድ ልብስ ይነትብና ምንም ዓይነት ብልሽት ሳይደርስበት መገኘቱ ግዲያው በህወሃት ዘመነ መንግስት ስለመፈፀሙ ጥሩ ማስረጃ ነው። ለህወሃት ሰው መግደል ሥራ እንጂ ወንጀል አይደለም። በህወሃት ነፍሰ ገዳይ ይሞገሳል ይሾማል እንጂ አይወቀሰም አይጠየቅም። የስድስቱ ሰዎች አስከሬን ሲገኝ መንግስትነኝ የሚለው ህወሃት አይቶ እንዳላየ መሆን ብቻ ሳይሆን ሌሎች አካላትም የሥፍራውን ሚስጢር እንዳያዩ ከልክሏል።በቁጥጥሩ ሥር ያሉ መገናኛ ብዙሃንም ዜናውን እንዳይናገሩ ታግደዋል። ህወሃት ከሚሰራቸው አስገራሚ ወንጀሎች መካከል አንዱይሄው ነው። ይሄ ግድያ በሌላ አካል ተፈፅሞ ቢሆን ኑሮ በረከት ስምዖንና እና ሺመልስ ከማል እየተፈራረቁ ያደነቁሩን ነበር።ይሄ የራሳቸው የእጅ ሥራነውና አይነገርም። የሄንንም የሚናገር እንደ ኢሳት ያለ ነፃ ሚዲያ ካለም ይታፈናል። አሸባሪም እየተባለ ይፈረጃል።

ግንቦት ሰባት የፍትህ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ እነዚህ ዜጎች በህወሃት ተግድለው እንደተጣሉ ያምናል። ውሎ አድሮ እውነቱ እስከሚወጣ ድረስ ግን ዜጎች በሙሉ ይሄን ግድ በተመለከተ መረጃ የመሰብሰብና የማሰረጫት ሥራችውን አጠናክረው እንዲቀጥሉ እናሳስባለን። ይሄን ወንጀል የፈፀሙ አካላት መጠየቅ አለባቸው። የዜጎች ደም እንዲሁ በከንቱ ፈሶ መቅረት የለበትም።

ለኢትዮጵያ ህዝብ መብትና ጥቅም እንታገላለን የሚሉ የፖለቲካና የስቪክ ድርጅቶች እንዲሁም ለሰው ልጆች የሰብአዊ መብት የሚሟገቱ ሁሉ የተገኘው አስከሬን በአስቸኳይ ተመርምሮ ማንነታቸው ለቤተሰቦቻቸውና ለወዳጅ ዘመዶቻቸው እንዲገለጽ፤ ተጨማሪ አስከሬን ሊገኝ ይችላል በሚልስጋት የመንገድ ቁፋሮውን ከሰዎች እይታውጪ ለማካሄድ እንዲቋረጥ የተደረገው ሥራ ለህዝብ እይታ ግልጽ በሆነመንገድ በአስቸኳይ እንዲጀመር የመጠየቅ ሃላፊነታቸውን እንዲወጡ ግንቦት 7 ያሳስባል::

በዚህ አጋጣሚ ወያኔ ሥልጣን ከተቆጣጠረበት ጊዜጀምሮ በሱማሌ፣ በጋምቤላ፣ በአዋሳ፣ በጎንደር፣ በአዲስ አበባና ሌሎች የአገራችን ክፍሎች በጠራራ ጸሃይ ካስጨፈጨፋቸው በተጨማሪ በፖለቲካ እምነታቸው ምክንያት ታግተው በየእሥርቤቱ የተወረወሩትንና ከታገቱበት ዕለት ጀምሮ እስከ ዛሬ የደረሱበት ያልታወቁ ወገኖቻችንን ዝርዝር በአስቸኳይ ያሳውቅ ብለን አንመክረውም።እኛ ግን ህወሃት የደበቀውን ወንጀል ሁሉ ህዝብ እንዲያውቀው ለማድረግ ያለምንም ማቅማማት ጠንክረን እየሰራን ነው። መንግስት ነኝ ብሎ በሥልጣን ላይ የሚወጣ ማንኛውም አካል የህዝብ አገልጋይ እንጂ ነፍሰገዳይ እንዳይሆን የጀመርነው ትግል ተጠናክሮ ይቀጥላል።

እንግዲህ ህወሃት በህዝባችንና በአገራችን ላይ የሚፈጽመውን ሰቆቃ ለማስቆም ግንቦት 7 የጀመረውን የነጻነት ትግል አጠናክሮ እንደሚቀጥል እያስታወቅን እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ እንዲህ በየቦታው ተገድሎ ከመጣል ራሱን ለመታደግ ሲል የነፃነቱ ትግል አካል እንዲሆን ጥሪያችንን አሁንም ደግመን እናቀርባለን።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !!!**

## ወያኔ የአገሪቱ ባለስልጣኖች ለኢሳት ቴሌቪዥንና ሬድዮ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ነው የሚል ምክንያት መሰጠቱ ታውቋል። ባለስልጣናቱ ከኢሳት በተጨማሪ ለአሜሪካ ድምጽ እና ለአንዳንድ ስማቸው ያልተጠቀሰ ድረገጾችም መረጃ እንዳይሰጡ ታዘዋል። የኢትዮጵያን ህዝብ ላለፉት ሃያ ሀለት ዐመታት የመረጃ ጨለማ ዉስጥ አጉሮ የያዘዉ ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ አፍሪካን ጨምሮ ብዙ የአለማችን አገሮች ዉስጥ ህዝብ የመረጃ ማዕከል እየሆነ በመጣበት ግዜ ወያኔ ግን የኢትዮጵያን ህዝብ ከኢትዮጵያ ቴሌቪዥንና ሬድዮ ዉጭ ምንም ነገር እንዳይሰሙ ለማድረግ ጥረቱን ተያይዞታል። የኢትዮጵያ ቴሌቪዥንና ሬድዮ የለየላቸዉ የወያኔ የዉሸትን የፕሮፓጋንዳ መሳሪዎች መሆናቸዉን ማንም የሰማቸዉና ያያቸዉ ዜጋ ሁሉ ስለሚያዉቅ እነሱ አቀረቡት የሚባለዉን መረጃ ህዝብ በመረጃነት እንደማይቀበለዉ ወያኔ እራሱ ያወቀዉ እዉነት ነዉ። ለዚህም ይመስላል ማድረግ የሚችለዉን ሁሉ አድርጎ ከደከመዉ በኋላ አሁን ለኢሳት ቃለመጠይቅ መስጠት በሽብርተኝነት ወንጅል ያስቀጣል ማለት የጀመረዉ። ይህ ሙከራዉም ቢሆን ከራሱ ባለስልጣናትና ከተቃዋሚ ፓርቲዎች አካባቢ ከፍተኛ ተቃዉሞ ገጥሞታል።

## ፋሽስት ወያኔ ለመጪው ዓመት ምርጫ . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

በቀጣይ ብዙ ትውልዶቻችን ከፍለን የማንጨርሰው በብድር የመጣ ሃብት እንኳ ቢሆን ለፋሽስት ወያኔ እስከሆነ ድረስ አላግባብ ይፈሳል። የሚፈለገው የሕወሃት ጊዜያዊ ዓላማ ከተሳካ በኋላ ግን ህብረተሰቡን የሚያስታውሰው ይለም። የመጨረሻው እዳ ከፋይም ይኸው ሕብረተሰብ ነው። በጣም አሳዛኝ ነው ይላሉ።

የመጭውን የወያኔ ምርጫ ውብ ለማስመሰልና ለማጭበርበር በአደረጃጀትና በስልጠና ስም እየተሰራ ያለው ድራማ ሁሉንም ሲቢል መስሪያቤቶች ያጠቃለለና ሰራተኞችንም ያካተተ እንዲሆን በከፍተኛ ሁኔታ እየተሰራበት ሲሆን ከዚህ በፊት የአመለካከት ጥራት ችግር አለባቸው ተብለው የሚጠረጠሩና አቋማቸው ያልተለየ ሰራተኞች ከፍተኛ ክትትል እየተደረገባቸው የዚሁ ስልጠና አካላት እንዲሆኑ መመሪያ ተላልፏል ተብሏል። ይህኑ ጉዳይ ለማስፈጸምም ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ ተመድቧል ተብሏል። ከዚህ በፊት በ1997 ዓ/ም ምርጫን በአሸናፊነት ለመወጣት ሲል ጥራታቸው በቅጡ ያልታየ የተለያዩ ሀገር አቃራጭ መንገዶችን ጨምሮ በየከተሞች የኮንዶሚኒየም ቤቶች ግንባታን በማፋጠን ልማታዊ መንግስት ነኝ ለማለት የሞከረው ፋሽስት ወያኔ ምንም እንኳ በጉልበቱ በሃይል ውጤቱን ቢገለብጠውም በሕዝብ ሚዛናዊ ፍርድ ከጫዋታ ውጭ በመሆን በምርጫ መረታቱ አይዘነጋም።

## የቻይና ኤክስፖርት ባንክና ኤክስፖርት ክሬዲት ኢንሹራንስ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

በአሁኑ ጊዜ 14 የቻይና ኩባንያዎች ከኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን በጨረታ ሥራ አግኝተው በመሥራት ላይ የሚገኙ ቢሆንም፡ የቻይና መንግሥት ፋይናንስ ለሚያደርጋቸው ፕሮጀክቶች ግልጽነት ያለው አሠራር ባለመኖሩና ኢትዮጵያ ውስጥ የቆዩ የቻይና ኩባንያዎች ብቻ ሥራ የሚያገኙበት አቅጣጫ መቀየሱ እንደሚያሳስባቸው፣ ሁለቱ የፋይናንስ ተቋማት በደብዳቤያቸው ገልጸዋል። ቻይና የረዥም ጊዜ ብድርና በአጭር ጊዜ የሚመለሱ ብድሮችን ለኢትዮጵያ ስትሰጥ የቆየች ሲሆን ፋይናንስ የምታደርጋቸውን ፕሮጀክቶች የሚገነቡት የቻይና ኩባንያዎች ቢሆኑም፣ ኩባንያዎቹ ሥራውን የሚያገኙት ከጉጅሌው አገዛዝ ባለስልጣናት ጋር በመመሳጠር ያለጨረታ በመሆኑ ምክንያት፣ ሌሎች የቻይና ኩባንያዎች ውድድር ባለመኖሩ ተበድለናል በማለት ቅሬታቸውን አሰምተዋል።

ከዚህ በተጨማሪም የቻይና የፋይናንስ ተቋማት አሁን ያለው አሠራር ለሙስና በር የሚከፍት በመሆኑ ባስቸኳይ ሊታረም እንደሚገባው አሳስበዋል። ከዚህ ቀደም በተከታታይ እንደዘገብነው ከቻይና ኩባንያዎች ጋር በመመሳጠር ከፍተኛ የሆነ የሀገር ሀብት በመዝረፍ ላይ የሚገኙት በሌቦች አለቃው በሳሞራ የኑስ የሚመሩት የወያኔ የጦር አዛዦችና ሌሎችም የህውአት ቁንጮ ባለስልጣናት ቡድን መሆኑ ይታወቃል።

## በጅምላ ገድሎ በጅምላ መቅበር ወያኔ ተወልዶ ያደገበት ሙያዉ ነዉ

በወያኔ ዘርኝነት፤ ጎጠኝነትና ወደር የለሽ ጭቆና ከሁለት አስርተ አመታት በላይ ጀርባዉ የጎበጠዉ የኢትዮጵያ ህዝብ ባለፉት ሁለት ወራት ዉስጥ በሁለት እጅግ አስቀያሚና ዘግናኝ በሆኑ የታሪክ ምዕራፎች ዉስጥ አልፏል። ለወትሮዉ በወርሃ ህዳርና ታህሳስ፤ ህዳር ሚካኤልንና የገና በዐልን እያከበረ አጆቹን ወደ ፈጣሪዉ የሚዘረጋዉ የኢትዮጵያ ህዝብ፤ ዘንድሮ ከእነዚህ ሁለት የቆዩ ባህሎቹና ወጎቹ ፈቀቅ ብሎ በሁለት ክብሩን ባዋረዱና ማንነቱን ጥያቄ ዉስጥ በከተቱ ከስተቶች ልቡ ቆስሎ ከራሱ ጋር ሲነታረክ ሰንብቷል። የፈጠረዉን አምላክ መለምን እንጂ በፈጣሪዉ አማርሮ የማያዉቀዉ የኢትዮጵያ ህዝብ . . . የሚያስብልኝ መንግስት እንደለሌለኝ አዉቃለሁ፤ አምላኬ ግን በፍጹም አይረሳኝም። ምነዉ ቅዱስ ሚካኤል አንተና ሰይፍህ እያላችሁ እንዴት እንዲህ ይደረጋል አንዴ . . . እያለ በምድራዊዉም በሰማያዊዉም መንግስታት ላይ የመረረ ጩኸቱን አሰምቷል።

በህዳር 2006 ዓም የኢትዮጵያ ህዝብ አገራቸዉ ዉስጥ የስራ ዕድል ተነፍገዉ ስራ ፍለጋ ወደ ሳዑዲ የተሰደዱ ወገኖቹ በሳዑዲ ፖሊስና ህዝብ ከፍተኛ በደል ሲፈጸምባቸዉ ተመልክቶ በኃዘንና በቁጭት ልቡ በግኗል። በተለይ ወንዶች ልጆቹ ፈለጊ እንደሌለዉ እንስሳ በየአደባባዩ ሲረገጡና ሲደበደቡ፤ ሴቶች ልጆቹ ደግሞ በየማጀቱ ሲደፈሩ ተመልክቶ ለህዝብና ለአገር ለሚያስቡ አስተዋይና ጨዋ መሪዎች ባለመታደሉ በባዕድ አገር ዉስጥ በደረሰበት ዉርደትና መከራ በአለም አቀፍ ደረጃ ጩኸቱን አሰምቷል።በዚሁ በ2006 ዓም በታህሳሰ ወር አጋማሽ ላይ ደግሞ የኢትዮጵያ ህዝብ በተለይ ብርድ ልብስ ተጠቅልሎ የተጣለ የሰዉ ልጅ አጽም ቀርቶ በስመአብ ተብሎ የታረደ በሬ ስጋም ማየት በማይፈልግበት በገና ፆም ወቅት የገዛ ወገኖቹ አጽም በመንገድ ቆፋሪዎች ከመሬት ዉስጥ እየተጎተተ ሲወጣ አይቶ በቆሰለ ልብና በነደደ አንደበት "እባክህ ፈጠሪ ወይ ዉረድ ወይ ፍረድ" እያለ ከወያኔ ጋር ከመኖር የፈጣሪን ፍርዱን አለዚያም ዳግም ምጽአቱን ተመኝቷል።

ባለፉት ሁለት ወራት ሳዑዲ አረቢያ ዉስጥ በሚገኙ ኢትዮጵያዉያን ወገኖቻችን ላይ የደረሰዉ ግፍና መከራ ድፍን ህዳርንና ታህሳስን በአለም ዙሪያ በአራቱም ማዕዘን የሚኖሩ ኢትዮጵያዉያንን ያሰባሰበ፤ ያነጋገረ፤ ያበሳጨ፤ ያስቆጨና አንጀት ያሳረረ ጉዳይ ነበር። አዎ የ2006 ህዳርና ታህሳስ አገር ዉስጥም ካገር ዉጭም ለምን መጡ የሚያሰኙ የቀን ጎደሎዎች ነበሩ። የወገኖቹ በባዕድ አገር አላግባብ መታሰር፤መደብደብና መገደል ያበሳጨዉ የኢትዮጵያ ህዝብ ከዚህ ሀዘኑና ብስጭቱ ሳይላቀቅ ነበር ባለፈዉ ታህሳስ 18ትና 19 ቀን ሌላ አሳዛኝና አስደንጋጭ ዜና የጭንቅና የመከራ ጓዳ የሆነችዉን መዲናችን ከአዲስ አበባን እንደ ሐምሌ ጨለማ የከበባት። ደርግን አሸንፈዉ ስልጣን ሲይዙ ደርግ ገድሎ የቀበረዉን አስከሬን መቃብር እየቆፈሩ ያወጡት የወያኔ መሪዎች እነሱም በተራቸዉ በጅምላ ገድለዉ በብርድ ልብስ እየጠቀለሉ የቀበሯቸዉን ኢትዮጵያዉያን አስከሬን ዬት እንደቀበሩት እንኳን ሰለማያዉቁ እነሱ እራሳቸዉ እየቆፈሩ አዉጥተዉ ወንድሞቹና እህቶቹ እንደወጡ የቀሩበትን የኢትዮጵያን ህዝብ አንጀት እንደገና አቁስለዋል።

እዚህ ላይ አንድ እጅግ በጣም ሊያሳስበንና ሊያስጨንቀን የሚገባ ነገር ቢኖር ባለፈዉ ሳምንት ከስድት ኪሎ ወደ ፈረንሳይ ለጋሲዮን በሚወስደው መንገድ ላይ በሚገኘው የጃንሜዳ ጦር ካምፕ አካባቢ በብርድ ልብስ እንደተጠቀለለ የተገኘዉ የ6 ሰዎች አጽም ሊገኝ የቻለዉ ሆን ተብሎ የጅምላ መቃብር ለማግኘት በተደረገ ቁፋሮ ሳይሆን በአጋጣሚ ነዉ። ይህ የሚያሳየን አዲስ አበባን ጨምሮ በብዙ የአገራችን አካባቢዎች ዉስጥ መረጃ የተሰበሰባበቸዉንና የሚጠረጠሩ ቦታዎችን የኢትዮጵያ ህዝብ ከአለም አቀፉ ህብረተሰብ ጋር ተባብሮ እየቆፈረ መፈተሽ ቢጀምር ወያኔ ጭካኔዉን ሊያሳየን ከሞከረዉ ከደርግ ስርዐት ጋር ምንም የማይለያይ ጨካኝና አረመኔ ስርዐት ለመሆኑ ማንም ማስተባበል የማይችለዉ ተጨባጭ ማስረጃ ይገኛል ብለን እናምናለን።

የወያኔ ዘረኞች አዲስ አበባን በተቆጣጠሩ ማግስት ስራችን ብለዉ የጀመሩት ደርግ የሰለበዉን የኢትዮጵያን ህዝብ ሞራል ማደስ ወይም በሶሻሊዝም ስም የደቀቀዉን የአገራችንን ኤኮኖሚ መገንባት አልነበረም። የደርግ ሰርዐት አንደ ገለባ ሲበተን አብሮት የተበተነዉ የቀድሞ የኢትዮጵያ መከላከያሰራዊትም ቢሆን እንደጠላት የሚመለከቱት ኃይል ስለነበር ይህ ለእናት አገሩ ዳር ድንበር መከበር ደሙን ያፈሰሰ ሰራዊት የሚበላና የሚቀመስ አጥቶ ወደ መንገድ ላይ ለማኝነት ሲቀየር ሌላ ቢቀር ጡረታዉን እንኳን ለማስከበር ያደረጉለት ምንም ነገር አልነበረም። ወያኔዎች ስልጣን እንደጨበጡ የደረጉት አቢይ ነገር ቢኖር ከክፍለ ሀገር ክፍለ ሀገረ እየዞሩ ደርግ በቀይ ሽብርና በሌላም ሌላ ግዜ ገድሎ የቀበራቸዉን ሰዎች መቃብር እየቆፈሩ አጽም መሰብሰብ ነበር። በወቅቱ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በተከታታይ እንደተመለከትነዉ የወያኔ ጉድጓድ ቆፋሪዎች የሰነበተ መቃብር እየከፈቱና አጽም እየሰበሰቡ ደርግ ምን አይነት ጨካኝ ነብሰ ገዳይ እንደሆነ ለአመታት የምናዉቀዉን እዉነት እንደገና እንድናዉቀዉ አድርገዉናል። በዚህ ከአንድ አመት ከመንፈቅ በላይ በዘለቀዉ የወያኔ መቃብር ቁፋሮ ወያኔ የቀድሞዉን ንጉስ የቀዳማዊ ኃ/ስላሤን ጨምሮ የብዙ ሰዎችን የመቃብር ቦታ እየቆፈረ እሱ ለፖለቲካ ፍጆታዉ የሚፈልጋቸዉንና በተለይ ደግሞ የኔ ናቸዉ የሚላቸዉን ሰዎች አጽም እየለቀመ አንደገና በክብር እንዲቀበሩ ሲያደርግ ሌሎቹን የደርግ ሰለባዎች ደግሞ ምሶ ያወጣዉን አፈር አንደገና መልሶባቸዋል። እንደዚህ አይነት ጉድ የተመለከትነዉ ከሃያ ሁለት አመታት በፊት ወያኔ ኢትየጵያን ሲቆጣጠር ነበር።

ባለፈዉ ሳምንት አዲስ አበባ ዉስጥ መንገድ የሚሰሩ ሰዎች ለራሳቸዉ ጉዳይ መሬት ሲቆፍሩ ከተጠቀለሉበት የደብረ ብርሀን ብርድ ልብስ ዉስጥ እየዘለሉ ወጥተዉ "የፍትህ ያለህ" እያሉ ሲጮኹ የሰማናቸዉ አጽሞች ወያኔ በእኔ ዘመነ መንግስት ሰዉ በሰዉነቱ ይከበራል እንጂ እየተጎተተ አየገደልም ብሎ ከማለ በኋላ በራሱ በወያኔ በግፍ እየተጎተቱ ተገድለዉ የተጣሉ ዜጎች አጽም ነዉ። ይህንን በታሪካችን ታይቶም ተሰምቶም የማይታወቅ ጉድ በስፍራዉ ተገኝተዉ የተመለከቱ የአይን ምስክሮች እንደተናገሩት ቦታዉ ዘመናዊ የመቆፈሪያ ማሽኖች በመቆፈር ላይ እያለ በመጀመሪያ አራት አስከሬኖች በብርድልብስ እንደተጠቀለሉ ተንከባለዉ ወደላይ ሲወጡ የታዩ ሲሆን፤ በሁኔታዉ የተደናገጡት ቆፋሪዎች ስራቸዉን አቋርጠዉ ወደ ቤታቸዉ ከሄዱ በኋላ በነጋታው ረፋዱ ላይ በሌላ አቅጣጫ ሌላ ቁፋሮ ሲያደርጉ አሁንም እንደገና በተመሳሳይ ሁኔታ በብርድ ልብስ የተጠቀለሉ ስድስት አስከሬኖች አግኝተዋል።

አንድ አስከሬኖቹ በተገኙበት አካባቢ በብዛት ተገኝቶ ሁኔታዉን ይመለከት የነበረዉን ህዝብ ለማባረር ወታደሮቹን አስከትሎ የመጣ ከፍተኛ ወታደራዊ የጦር መኮንን "ይህ ግቢ ሶስት ስርዓቶችን ያገለገለ በመሆኑ የማናቸው እንደሆነ ለማወቅ አይቻልም፤ ሆኖም ሰዎች በመሆናቸው ክቡር ናቸውና አፈር አልብሷቸው" በማለት የዘረኞቹን የወያኔ መሪዎች አይን ያወጣ ወንጀል ለመደበቅ ሲሞክር ተደምጧል። ሆኖም ሁኔታዉን በቅርብ ሆኖ የተከታተለዉም ሆነ በርቀት ሆኖ በምስል የተመለከተ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ወንጀሉ የሌሎቹ መንግስታት ሳይሆን የወያኔ መሆኑን ለመገንዘብ ግዜ አልወሰደበትም። አስከሬኖቹ በጅምላ የተጠቀለሉበት የደብረ ብርሀን ብርድ ልብስም ቢሆን እንኳን መሬት ዉስጥ ተቀብሮ ምስጥ፤ እርጥበትና ዘመን ተፈራርቀዉበት፤ አልጋ ላይ ህያዉ ሰዉ ለብሶትም ቢሆን ሃያ አመት ቀርቶ አምስት አመትም የሚቆየዉ የዛሬዎቹ የወያኔ መሪዎች ለብሰዉት አንደመጡት ቁምጣ በመርፌ ከተጠቋቆመ ብቻ ነዉ። ባለፈዉ ሳምንት አርብና ቅዳሜ አስር አስከሬኖችን እንዳቀፈ ከመሬት ዉስጥ ሲወጣ ያየነዉ ብርድል ልብስ የሚያሳየን ነገር ቢኖር ወያኔ በስልጣን ላይ እስካለ ድረስ ኢትዮጵያዉያንን በሚስጢር እየገደለ እንደ ቆሻሻ ዕቃ ዬትም ቦታ መጣሉን እንዳማያቆም ነዉ።

የአገራችን የኢትዮጵያ ህዝብ ለሀይማኖት የሚሰጠዉ ቦታ እጅግ በጣም ከፍተኛ ነዉ። በእስልምናዉ፤ በክርስትናዉም ሆነ በአይሁድ ሀይማኖቶች አስተምህሮ በሀይማኖት ዉስጥ ሁለቱ ዋና ዋና አካሎች እግዚአብሄርና ሰዉ ናቸዉ፤ ይህ የሚያሳየን ሰዉ ክቡር ፍጡር መሆኑን ነዉ። ወደዚህ አለም ሲመጣም ሆነ ይህችን አለም ሲለይ በከብር መጥቶ በክብር የሚሸኝ የሰዉ ልጅ ብቻ ነዉ። የኢትዮጵያ ክርስትና እምነት መሰረት ከሆነችዉ ከትግራይ ክልል የመጡት የዛሬዎቹ የኢትዮጵያ መሪዎች ግን ክርስትናዉን ብቻ ሳይሆን የራሳቸዉንም ሰዉ መሆን የረሱ ይመስላል። ሰዉን የመሰለ ክቡር ፍጡር በጅምላ ተገድሎ፤ በጅምላ ከተቀበረበት ቦታ በኮንስትራክሺን ሠራተኞች ከመሬት ዉስጥ እየተጎተተ መዉጣቱን የሰሙ የወያኔ መሪዎች ጉዳዩን አስመልክቶ አንድም ትንፍሽ ያሉት ቃል የለም። እነሱ ብቻ ሳይሆኑ በእነሱ ቁጥጥር ስር ያሉት የኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥንም እነማን እንደሆኑ፤ መቼ እንደሞቱና ማን እንደገደላቸዉ የማይታወቅ ሰዎች አስከሬን በብርድልብስ ተጠቅልሎ ሲገኝ ያንን ለስድብና ህዝብን ለመኮነን ቀኑን ሙሉ የሚከፍቱትን አፋቹዉን መክፈት አልፈለጉም። የሚገርመዉ እንደ አለባሌ ነገር ከተጣሉበት ቦታ ተጎትተዉ የወጡት አስከሬኖች ሁኔታና የተጠቀለሉበት ብርድልብስ ሙሉ በሙሉ ወንጀሉን ወያኔ ላይ ስለሚያመለክት ነዉ እንጂ የእነሱ እጅ የሌለበት ወንጀል ቢሆን ኖሮ የኢትዮጵያ ህዝብ አንድ ሳምንት ሙሉ ሌላ ዜና አይሰማም ነበር።

አገር ዉስጥም ሆነ በዉጭ አገሮች የሚኖረዉ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ባለፈዉ ሳምንት እንደ ዋዛ ከመሬት ዉስጥ እየተጎተቱ የወጡ ወገኖቹን አስከሬን ጉዳይ በቀላሉ መመልከት የለበትም። ወያኔ ስልጣን እጁ ከገባ ጀምሮ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዉያንን እያፈነ በየማጎሪያ ቤቱ አጉሯቸዋል። ከሰሞኑ ጃንሜዳ አካባቢ ያየነዉ ዘግናኝ ክስተት ስለእነዚህ ወያኔ በየድብቅ አስር ቤቶች አስሮ አድራሻቸዉ ስለጠፋ ዜጎቻችን ብዙ የሚለዉ ነገር ያለ ይመስለናል። እኛ ነን አድራሻቸዉ የጠፋ ሰዎች እያልን የምንጨነቀዉ እንጂ እነዚህ ወያኔ አስሯቸዉ አድራሻቸዉ የጠፋ ሰዎች ዬት እንዳሉ ጃንሜዳ አፉን ከፍቶ ነግሮናል። አዲስ አበባና በየከተማዉ የሚኖረዉ ህዝብ ስለወያኔ የጅምላ ግድያ የሚያዉቀዉ ብዙ ሚስጢር ይኖራል፤ በጅምላ ተገድለዉ በጅምላ የሚቀበሩ ሰዎችንም ጉዳይ በተመለከተ ማንም ሰዉ ሳያየዉና ሳያዉቀዉ የሚፈጸም ነገር አይመስለንምና ከአሁን በኋላ ጥረታቻን ሁሉ የወያኔ የጅምላ ግድያዎች በብሄራዊና በአለም አቀፍ አካላት እንዲመረመሩና ወንጀለኞቹ ለፍርድ እንዲቀርቡ ማድረግ መሆን አለበት። በዚህ ጉዳይ ላይ መረጃ ያላቸዉ ዜጎች መረጃዎቻቸዉን ማሰባሰብ፤ማደራጀትና ለሚመለከተቸዉ አካላት መስጠት ይኖርባቸዋል። ዬት እንደደረሱ ሳናዉቅ ባለፈዉ ሳምንት ሳይተሳብ በደብረህርሃን ብርድ ልብስ እንደተጠቀለሉ ከመሬት ዉስጥ የወጡ ዜጎቻችን ፍትህ ሳያገኙ ማንም ኢትዮጵያዊ እንቅልፍ ሊወስደዉ አይገባም።

## የዋሺንግት ዲሲና የአካባቢዋ ነዋሪዎች መሬታችን ለባዕዳን አይሰጥም አሉ

ባሳለፍነው ሳምንት የዲሲ የጋራ ግብረ ሃይል በመባል የሚታወቀው በሰሜን አሜሪካ ዋሽንግተን ዲሲና አካባቢው የሚገኙ ኢትዮጵያዊን ያስተባበረ ቡድን የወያኔ አገዛዝ ከኢትዮጵያ ቆርሶ ለሱዳን ድንበር የሰጠውን መሬት በተመለከተ የተሰማውን ቁጣ ገልተጿል። የዲሲ የጋራ ግብረ ሃይል ጸረ ኢትዮጵያ የሆነው ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ አባቶቻችን በደማቸው አስከብረው ያቆዩትን ያገራችንን ዳር ድንበር ለጊዜያዊ የፖለቲካ ጥቅም ሲል አሳልፎ መስጠቱ ግልጽ ነው ብሏል። ቡድኑ ባወጣው መግለጫ ኔ ሰሞኑን የአልበሽርን መንግስት ለማስደሰት እና ተባባሪው ለማድረግ ሲል ኢትዮጵያዊ ዜጎቻችንን ለዘመናት ከኖሩበት ቀያቸው በማፈናቀል 1200 ኪሎ ሜትር የሚሆን ክልል ለመለገስ እየተዘጋጀ ይገኛል ብሏል።ይህንን ህገወጥ ዳር ድንበር የመሸጥ ተግበር ለመላው የዓለም ህዝብ እና በተለይም ለሱዳን መንግስት እና ህዝብ ለማሳወቅ ዋሽንግተን ዲሲ በሚገኘው የሱዳን ኢንባሲ ፌብሯሪ 13 ቀን 2014 ዓመተ ምህረት ሰልፍ ለማድረግ ማቀዱን አስታውቋል።

## አትዮጵየዉያን በያሉበት የወያኔን "አንድ ለአምስት" አደረጃጀት እየተቃወሙት ነዉ

የቤተሰብ አባላት ድረስ የሚዘልቀው እና አምስት ለአንድ የተሰኘው የወያኔ አደረጃጀትን አስተመልክቶ በርካታ የህብረተሰብ ክፍሎች የወያኔ ፍርሃት ስር እየሰደደ መምጣቱን እና ማንኛውም የህብረተሰብ ክፍል የሚያደርገውን እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር መሻቱን ያሳያል ሲሉ አስተያየታቸውን በዚህ ሳምንት ገልጸዋል።

ይህን አደረጃጀት አስመልክቶ ወያኔ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ያሰፈነው አፈና የበለጠ ለማባባስ እና ህዝቡን መላወሻ ለማሳጣትሲል የፈጠረው ዘዴ መሆኑን በርካቶች አስተያየታቸውን የሰጡ ሲሆን ይህ አደረጃጀት ቤተሰብ ድረስ መዝለቁ የወያኔ የፍርሃት ደረጃ የቱን ያህል እንደደረሰ ያሳያል ብለዋል።

ሃገር ቤት የሚገኙ ሌሎች አስተያየት ሰጪዎች በበኩላቸው ህዝቡ ይህንን አደረጃጀት በመጠቀም ወያኔን ከስር መሰረቱ ለመገርሰስ ሊጠቀምበት እንደሚችል እና ህብረተሰቡን ጥልቅ ፍርሃት ውስጥ ለመክተት ያለመውን የወያኔን እቅድ ሊያከሽፈው እንደሚችል ተናግረዋል። የወያኔ ፍርሃት ህዝቡ ከገባበት ፍርሃት ብሷል እና ይህ አደረጃጀት ህዝቡን ጠርንፎ ለመያዝ የታለመ ስለሆነ ፍርሃታችንን አሽንፈን እንውጣ የሚል መልእክትም አስተላልፈዋል።

## የወያኔዉ ፍርደ ገምድል ፍርድ ቤት አሁንም የወገንተኛ እጁን በኦሮሞ ተወላጆች ላይ እንደጣለ ነዉ

የወያኔ አገዛዝ ካንጋሮ ፍርድ ቤት ባሳለፍነው ሳምንት 45 የሚሆኑ በኦሮሞ የነጻነት ግንባር አባልነት የተጠረጠሩ ዜጎች ላይየጥፋተኝነት ብይን በመስጠት እስከ 12 ዓመት ድረስ የሚደርስ ጽኑ እስራት ፈርዶባቸዋል።

የወያኔ ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አራተኛ ወንጀል ችሎት የተለያዩ የሽብር ሴራ ሊያከናውኑ ሲሉ ተደርሶባቸዋል በሚል የቀረበባቸውን ሀሰተኛ ክስ ያለምንም ማጣራት ተቀብሎ ጥፋተኛ ያለቸው ሲሆን ወዲያው እስከ 12 ዓመት የሚደርስ ጽኑ እስራት በመወሰን ወደ ወህኒ እንዲወርዱ አዟል።

የጥፋተኛነት ብይን ከተሰጣቸው እና የእስራት ቅጣት ከተወሰነባቸው 45 ዜጎች በተጨማሪ ሌሎች 18 ሰዎች አብረው
ተከሰው የነበረ ቢሆንም እና ተመሳሳይ ክስ እና ማስረጃ የቀረበ ቢሆንም 18ቱ በነጻ ሲለቀቁ 45ቱ ለምን ሊፈረድባቸው እንደቻለ ግልጽ አለመሆኑን የፍርድ ሂደቱን የተከታተሉ ምንጮች ገልጸዋል።

## አንድነት ፓርቲ ፀረ-ሽብር አዋጁን ማስቀየር የሚችል ድምጽ አሰባሰብኩ አለ

ፀረ-ሽብር አዋጁን በመቃወም "የሚሊዮኖች ድምፅ" በሚል መርሃግብር የህዝብ ፊርማ ሲያሠባስብ የቆየው አንድነትለፍትህና ለዲሞክራሲ ፓርቲ፤ ህጉን ለማሠረዝ የሚያስችል በቂ ድምፅ ማግኘቱን በዚህ ሳምንት አስታውቋል።ከ1ሚ. በላይ ፊርማ አሰባስቤአለሁ ያለው ፓርቲው፤ የህዝቡን ፊርማ በመያዝ ክስ እንደሚመሰርትም ገልጿል።ፓርቲው ለ3 ወራት ባካሄደው ፊርማ የማሰባሰብ ዘመቻ የፀረ ሽብር አዋጁን ለማሰረዝ የሚያስችል ድምጽ ማግኘቱን የገለፀው ፓርቲው አሁንም ድረስ በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን በኦንላይን እየፈረሙ በመሆኑ አጠቃላይ የፈራሚዎቹን ቁጥር መግለጽ ቢያዳግትም፣ እስካሁን ከ1 ሚሊዮን በላይ ፊርማ መሰባሰቡን አረጋግጠናል ብሏል። የጸረ ሽብር ህጉ ወያኔ እመራበታለሁ ብሎ ራሱ ካወጣው ህገ መንግስት ጋር እንደሚቃረን እና የህዝብን የመናገር እና ሃሳብን የመግለጽ ነጻነት ሆን ተብሎ ማፈን የወጣ ህግ መሆኑ ይታወቃል።

## በአባይ ግድብ ቦንድ ሽያጭ ስም ገንዘብ መሰብሰብ ያልተሳካለት ፋሽስት ወያኔ የሊዝ ዋጋን ማናሩ ተሰማ

በመላው የሀገሪቱ ክፍሎች ከገጠር እስከ ከተማ ከትንንሾቹ እቁቦች እስከ ታላላቅ ድርጅቶች ድረስ በአባይ ግድብ ስም በመለመን ብር ለማሰባሰብ አልሞ በእግር በፈረስ የተሯሯጠው ፋሽስት ወያኔ የልመናውን አድማስ በማስፋት በዓለም ዙሪያ በስደት የሚኖሩ ኢትዮጵያንን ለማማለል አሉኝ የሚላቸውን ቁንጮ የወያኔ አለቆችን ለልመና ቢያሰማራም ከአባይ በፊት ዘረኝነት፣ ፍትህ ማጣት፣ ወያኔ ሰራሽ የኑሮ ውድነት፣ አድሎዋዊነት፣ ጎጠኝነት ይገደብ የሚል መልስ በማግኘቱ ከየተከራያቸው አዳራሾች አፍሮ መባረሩ ይታወሳል። ይሁን እንጅ የልመናውን ዘዴ ወደ ሌላ አቅጣጫ በማዞር አርባ በስልሳ፣ አስር በዘጠና የሚባሉትን የመኖሪያ ቤቶች በመገንባት ሰበብ ገንዘብ የማሰባሰቢያ መነገዶችን የተጠቀመው ፋሽስት ወያኔ በዚህ መንገድም አንዳልተሳካለት ሲረዳ በተቀነባበረ መንገድ የሊዝ ዋጋን በማናር ዝርፊያ እንደጀመረ ተገልጿል።

ፋሽስት ወያኔ በአዲስ አበባ ከተማ አንዳንድ አካባቢዎች ለመኖሪያና ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውሉ ቦታዎች የሊዝ የጨረታ ዋጋ ላንድ ካሬ ሜትር እስከ 32000 ብር እንዲቀርብ በማቀነባበር በመዝረፍ ላይ እንደሆነ ታውቋል። "ማንነታቸውን ያላስደፈሩ፣ አመለካከታቸውን ያላስነጠቁ ውድ ኢትዮጵያዊያን ከየትኛውም የስራና የኢንቨስትመንት መስክ በሰበብ አስባቡ እየተገፉ እንዲወጡና የስራና ንግድ ቦታቸውም በልማት ሰበብ ለሊዝ እንዲወሰድ ይደረጋል። ያባትህ ቤት ሲዘረፍ አብረህ ዝረፍ በማለት ከወያኔ ጋር አብረው የዘረፉትንና በየዋህነት መሬት ለማግኘት የተሰለፉትን የዋሆች ደግሞ በእንደዚህ አይነቱ የሊዝ ጨረታ በመጠቀም መልሶ ይዘርፋቸዋል" ካሉ በኋላ "የወያኔ ጥቃት ጣምራ ነው። እውነተኛ ኢትዮጵያዊያንን ከኢኮኖሚው ማስለቀቅ አንደኛው ሲሆን በቦታቸው ደግሞ የኔ የሚላቸውንና ተቃውሞ የማያሰሙትን በመተካት የስልጣን ጊዜን ለማራዘም የሚረዱ ጥገት ላሞችን ማደራጀት ሁለተኛው ነው። ስለሆነም በዚህ የሊዝ ሰበብ ቦታውን ለማግኘት ስንቶቹን ኢትዮጵያዊያን አለመጠለያና የገቢ ምንጭ እንደበተናቸው ሁሉ ቦታውን መልሶ በሊዝ በመሸጡ በኩልም ተማሳሳይ እኩይ ስራዎችን በመስራት ከፍተኛ መጠን ያለው የዝርፊያ ገንዘብ ይሰበስብበታል ያላሉ።

ከዚህ በፊት በተለያዩ ጊዜያት ለልማት በሚል የስንቶቹን መኖሪያና የስራ ቦታ በሊዝ ስም ዝርፊያ በሚሰኝ ዋጋ በመሸጥ ገንዘብ ሲሰበስብ እንደነበረ ዓለም አቀፍ የዜና ማሰራጫዎችን ጨምሮ በተለያዩ የዜና አውታሮች ሲዘገብ መቆየቱ ይታወሳል።

## ከሳውድ አረቢያ የተባረሩ ዜጎች በችግር ላይ መሆናቸው ታወቀ

አገር ዉስጥና በአለም አቀፍ ደረጃ የደረሰበትን ከፍተኛ ጫና ለማስታገስ ሲል ብቻ "ዜጎችቼን በደስታ እቀበላለሁ" ብሎ ከአንድ መቶ ሃምሳ ሺ በላይ ዜጎችን ከሳዑዲ አረቢያ አገረ ዉስጥ እንዲገቡ ያደረገዉ የወያኔ አገዛዝ እስካሁን ድረስ ለተመላሽ ዜጎቻችን ምንም ያደረገዉ ነገር ባለመኖሩ የሳዑዲ ተመላሽ ወገኖቻችን ሳዑዲ ዉስጥ ይደርስባቸዉ ከነበረዉ በደል ባልተናነሰ ሁኔታ አሁንም ከፍተኛ ችግር ላይ መሆናቸዉን ዘጋቢዎቻችን ከአዲስ አበባ የላኩልን ዜና ገለጸ። መንግስት ከ150 ሺ በላይ ተመላሽ ዜጎችን ወደ ተወለዱበት አካባቢ መልሶ በመላክ በቡድን በማደራጀት የስራ እድል እንደሚፈጥር ያስታወቀ ቢሆንም ማስታወቂያዉ በዜና ማሰራጫዎች ከመነገሩ ዉጭ ብዙም ሌላ ምንም የፈየደዉ ነገር እንደሌለ ብዙዎች ተመላሾች ዝግጅት ክፍላችን ድረስ ስልክ እየደወሉ በመናገር ላይ ናቸዉ። አብዛኛዎቹ የሳዑዲ ተመላሽ ወገኖቻችን ወደ ወደ ተወለዱበት አካባቢያቸው ከተመለሱ በኋላ ለከፍተኛ ችግር መዳረጋቸው ታውቋል። ሰሜን ሸዋ አካባቢ በርካታ ስደተኞች መመለሳቸውን የገለጹት ጉዳዩን በቅርበት የሚከታተሉ አንድ ሰው፣ ተመላሾቹ በአነስተኛ እና ጥቃቅን እንዱስትሪዎች ትደራጃላችሁ በሚል ተስፋ ቢመጡም፣ ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

### የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

**መካከኛ ሞገድ**:- በ 358 MB, በ 837 kHz
**አጭር ሞገድ**:- በ 31 MB በ 9700 KHz
በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz
በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

### ውድ አንባቢዎቻችን

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## የመንግስት የፕሬስ ተቋማት የግል መጽሄቶችን በጽንፈኝነት ፈረጁ

የወያኔ ርካሽ ፕሮፓጋንዳ ተሸካሚ የሆኑት ኢትዮጵያ ዉስጥ የሚገኙ መንግስታዊ የፕሬስ ድርጅተችና የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት በሚል ስያሜ የሚታጠራዉ ነገር ግን ምንም ኢትዮጵያዊነት የማይታይበት ድርጅት በጋራ ባካሄዱት ጥናት ከወያኔ ግድያና አፈና ተርፈዉ በመንገዳገድ ላይ የሚገኙትን ነጻ ጋዜጠኞችንና የግል ፕሬስ አባላትን ጽንፈኞች ናቸዉ ብለዉ መኮነናቸዉ ተሰማ። እነሱ እራሳቸዉ በወያኔ ታፍነዉ ጻፉ የሚባሉትን ብቻ የሚጽፉትና ተናገሩ ተብሎ ከተነገራቸዉ ዉጭ ምንም መናገር የማይችሉት የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎትና መንግስታዊ የፕሬስ ድርጅቶች ለነሱ ነፃ መዉጣት ጭምር የሚታገሉትን የግል ሜድያ አባላትን ጽንፈኞች ናቸዉ በማለት ወያኔ በሰበብ ባስባቡ እርምጃ እንዲወስድባቸዉ ጥሪ አድርገዋል። በእነዚህ የገዢዉ ስርዐት አቀንቃኞች በሆኑት ድርጅቶች ጽንፈኞች ናቸዉ ተብለዉ ከተኮነኑትና አገር ውስጥ ከሚታሙት መጽሄቶች መካከል አዲስ ጉዳይ፣ ፋክት፣ ሎሚ፣ ቆንጆ፣ ጃና፣ እንቁ እና ሊያ የተባሉ መጽሔቶች ይገኙበታል።

አዲስ ዘመን ጋዜጣ ባለፈዉ ረቡዕ ታህሳስ 30 ቀን 2006 ዕትሙ ላይ ካላይ ስማቸዉ የተጠቀሱትን መጽሄቶችና ጋዜጦች የጽንፈኛ ፖለቲካ ፓርቲዎች ናቸዉ ከማለታቸዉም በላይ በተሳሳቱ መረጃዎች ህዝብን ያሳስታሉ ሲለል የአብዬኢን ወደ እምዬ መሰል ንግግር ተናግሯል። መጽሄቶቹ የተሳሳቱ=ተ መረጃ ለህብረተሰቡ በማቀበል ሕዝቡ በስርአቱ ላይ እምነት አጥቶ ለአመጽ እንዲነሳሳ የሚያደርጉ ዘገባዎችን ያቀርባሉ ብሏል። በጥናቱ መጽሔቶቹ የመንግስትን ኃላፊዎች የግል ስብዕና እንደሚነኩ፣ የአመጽ ጥሪዎችን እንደሚያሰሙ፣ ሽብርተኝነትን እንደሚያበረታቱ፣ የፖለቲካ ስርዓቱን እንደሚያጨልሙ፣ ኢኮኖሚ ዕድገቱን እንደሚነጻ ከዱ፣ ህገመንግስቱን እንደሚጥየግኢ የፕሬኢሱ በዝርዝር አቅርቧል። መንግስት መጽሄቶችን በጽንፈኝነት በመፈረጅ ምናልባትም ከ2007 ምርጫ በፊት እንዲዘጉ ሊያደርግ ይችላል ሲል አንድ ያነጋገርነው ጋዜጠኛ ተናግሯል።

“መንግስት ምንም አይነት እርሱ ከሚያራምደው አጀንዳ ውጭ የተለየ ድምጽ መስማት አይፈልግም” የሚለው ጋዜጠኛውም፣ መጽሄቶችን በተለያዩ መንገዶች በመፈረጅ ከገበያ ለማውጣት ያሰበ ይመስላል ሲል አክሎአል። ኢትዮጵያ የፕሬስ መብቶችን በማፈንና ጋዜጠኞችን በማሰር ግንባር ቀደም ተጠቃሽ ናት። ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ፣ ርእዮት አለሙ፣ ውብሸት ታየ፣ የሱፍ ጌታቸውና ሌሎችም ሀሳባቸውን በመግለጻቸው ብቻ መታሰራቸው ይታወቃል። ከምርጫ 97 በሁዋላ እጅግ ዝነኛ ጋዜጣ ሆነ የወጣው ፍትህ ጋዜጣም በመንግስት ጫና ከገበያ እንዲወጣ ተደርጓል። በጋዜጣው ላይ ሲሰሩ የነበሩት ታዋቂ ጋዜጠኞችም በተለያዩ ክሶች ሲዋከቡ ቆይተዋል።

## ሰማያዊ ፓርቲ ሀሳቤን ለመግለጽ የማንም ፈቃድ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

**አንድ የአዲስ አበባ ነዋሪ** ሰማያዊ ፓርቲ የወሰደዉን እርምጃ አደንቀዉ ቀድሞዉንም ቢሆን ወያኔን ገና ከጧቱ በአፋችን መቃወም ብቻ ሳይሆን “እምቢ አንገዛም” ብለን ቢሆን ኖሮ ዛሬ እዚህ ደረጃ አንደርስም ነበር ብለዋል። ወያኔ ዜጎችን እንዳሰኘዉ እያሰረና ጉዳያቸዉ በፍርድ ቤት ታይቶ ዉሳኔ ያልተሰጠባቸዉንሰላማዊ ግለሰቦች በሚቆጣጠራቸዉ የመገናኛ ብዙኃን አማካይነት እኢደ ጥፋተኛ ይኮንናል ያሉት እኚሁ ግለሰብ ወያኔ ለሌሎች ማስጠንቂያ ከመስጠቱ በፊት እራሱ ህግ ማክበር አለበት ብለዋል። “ኢሳት” የተባለ የመገናኛ ብዙሃን በኢትዮጵያ መንግስት በሽብርተኝነት ከተፈረጀ ድርጅት የገንዘብ ድጋፍ እንደተደረገለትና በሰላማዊ መንገድ የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች በተለይም ሰማያዊ ፓርቲ በዚህ የመገናኛ ብዙሃን እንዳይጠቀም የማስጠንቀቂያ ዛቻ ተላልፎለታል” ሲል ያስታወሰው ሰማያዊ ፓርቲ፣ ይህ አስፈራሪ አካል ራሱን ሕግ አውጭና ሕግ ተርጓሚ በማድረግ የዚህች ሐገር ዜጎች ሃሳባቸውን የሚገልጹበትንና የማይገልጹበትን የመገናኛ ብዙሃን እየወሰነላቸውና እየመረጠላቸው ይገኛል፣ ብሎአል።

የገዥው ቡድን ሰዎች ሀሳብን በሃሳብ ማሸነፍ እንደማይችሉ ስለሚያውቁት የቀራቸው አማራጭ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ሃሳባቸውን የሚያሰራጩባቸውን መንገዶች መዝጋት ብቻ መሆኑን ፓርቲያችን ይገነዘባል ያለው ሰማያዊ ፓርቲ፣ ማንም አካል በሕግም ሆነ በሞራል ተጠያቂ የሚሆነው የሚያስተላልፈው መልዕክት ይዘት የሌሎችን ዲሞክራሲያዊና ሞራላዊ መብት የሚጋፋ መሆን አለመሆኑ እንጂ ገዥው ቡድን በጠላው ወይም በወደደው የመገናኛ ብዙሃን መልዕክቱን ማስተላለፉ አይደለም” ሲል አቋሙን ግልጽ አድርጓል። መልዕክትን የገዥው ቡድን ሰዎች በጠሉት የመገናኛ ብዙሃን ማስተላለፍ በራሱ ወንጀለኛ ወይም ሽብርተኛ ለማድረግ የሚያበቃ ምንም ዓይነት የሕግ መሰረት እንደሌለውም ገልጿል።

ፓርቲው በመጨረሻም” ሰማያዊ ፓርቲ መልዕክቱን የሚያስተላልፍበትን መገናኛ ብዙሃን ማንም አካል እንዲመርጥለት ወይም በዚሁ አጋጣሚም የፓርቲያችንን መልካም ስም በሃሰት ለማጉደፍ የተሰነዘሩ ቃላትን በቀላሉ የማንመለከታቸው መሆኑን ሕግ ባለበት ሐገር ራስን ከሕግ በላይ በማስቀመጥ ማንንም አካል መፈረጅና ስም ማጉደፍ በሕግ የሚያስጠይቅ መሆኑን የዘጋቢ ፊልሙ ባለቤቶች እንዲያውቁትና ወደፊትም ተመሳሳይ ድርጊት ከመፈፀም እንዲቆጠቡ እናሳስባለን።” ብሎአል። በአገር ውስጥ የሚንቀሳቀሱት ሰማያዊ ፓርቲ እና አንድነት ፓርቲ በኢሳት ላይ ቀርበው አቋማቸውን እንዳይገልጹ መንግስት ሰሞኑን ምክር አዘል ማስጠንቀቂያና ማስፈራሪያ በኢቲቪ አማካኝነት መስጠቱ ይታወሳል። ከመጪው ምርጫ ጋር ተያይዞ ኢሳት ገዢውን ፓርቲ ጨምሮ በአገር ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ፓርቲዎች ፕሮግራሞቻቸውንና መልእክቶቻቸውን በነጻ እና ያለገደብ የሚያስተላልፉበትን አሰራር በመቀየስ ላይ ነው።

ይህ በእንዲህ እንዳለ አድራሻዉ እዚያዉ አዲስ አበባ ዉስጥ የሆነዉ አንድነት ለፍትህና ለዲሞክራሲ ፓርቲ ለሚዲያዎች ሃሳብን መግለጽ አሸባሪነት አይደለም ሲል መግለጫ አወጣ። አንድነት ለፍትህና ለዲሞክራሲ ፓርቲ ባወጣው መግለጫ ሰሞኑን ኢቲቪ ባዘጋጀው ዶክመንተሪ ላይ “መቀመጫውን በውጭ በማድረግ የተለያዩ ዜናዎችንና ፕሮግራሞችን በማሰራጨት የሚታወቀውን ኢሳት(ESAT) ሬዲዮ እና ቴሌቪወጠዥን ጣቢያ ላይ ፓርቲያችን ለአባላቱ እና ለደጋፊዎቹ መልዕክት ማስተላለፉን እንዲሁም እንደፓርቲ ለማንኛውም ሚዲያ የፓርቲያችንን ሰላማዊ እንቅስቃሴ በተመለከተ ስንጠየቅ የመመለስ መብታችንን በሚጋፋ መልኩ የፓርቲያችንን አቋም አዛብቶ ለማቅረብ ሞክሯል” ብሎአል።

“ኢህአዴግ በሚጠላቸው እና በሚያጥላላቸው ሚዲያዎች ሃሳብን መግለፅ በየትኛውም መመዘኛ አሸባሪነት ሊሆን አይችልም” ያለው አንድነት፣ የኢህአዴግ መንግስት ሲያስነጥሰው ከሚያለቅሱለት የፕሮፓጋንዳው ፍጆታዎች ከሆኑት ሚዲያዎች ውጪ የኔ ያልሆኑ የሌላ ናቸው ብሎ የሚያምን በመሆኑም ፍረጃው ህጋዊ አግባብነትም ሆነ መረጃ የሌለው ባዶ ፍረጃ” ነው በማለት የመንግስትን ማስጠንቀቂያ አጣጥሎታል።“ኢህአዴግን የህዝብን ጥያቄ በዶክመንተሪ ጋጋታ መመለስ እንደማይቻል” ልናስታውሰው ብንሞክርም፣ አሁንም በዶክመንተሪ ፊልሞች ስም ከማጥፋት፣ ከመፈረጅና ከማስፈራራት መላቀቅ አልቻለም። ” ሲል ፓርቲው አክሎ ገልጿል።አንደነት በመጨረሻም ” ህገ መንግስታዊ መሰረት የሌለው ቢሆንም እንኳ ቢያንስ ራሳቸው ላወጡት ህግ ታምነው ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በማቅረብ ሳያስወስኑ አንድን የሚዲያ ተቋም ያውም ለአንድ አላማ የተቋቋመ የፀረ-ሽብር ግብረሃይል ‹‹የአሸባሪ ድርጅት ልሳን ነው›› ወይም ‹‹አሸባሪ ነው›› በማለት ሲፈርጅ ስናይ አሁንም የሀገራችን ፖለቲካ ፓርቲና መንግስት የተደበላለቁበት፣ አንድ ድርጅት እንደፈለገው የሚፈርጅበት ስርዓት እንዳለ የሚጠቁም ነው” ብሎአል።

## ከሳውድ አረቢያ የተባረሩ ዜጎች በችግር ላይ

. . . ( ከገጽ 4 የዞረ )

ቃል የተገባላቸው ነገር ባለመፈጸሙ ለከፍተኛ ችግር ተዳርገዋል። አንዳንድ ሴቶች በሴተኛ አዳሪነት እየተሰማሩ እንዲሆነ የገለጹት እኚሁ አግለሰብ፣ ሌሎች ደግሞ ከቤተሰቦቻች ጋር ሳይቀር ግጭት ውስጥ እየገቡ መሆኑን ተናግረዋል።ዘ ኒው ዮርክ ታይምስ የሚባለው ታዋቂው ጋዜጣ ባወጣው ሪፖርት ተመላሾቹ ህይወትን ለመላመድ ቀላል እንደማይሆንባቸው የተለያዩ ሰዎችን አነጋግሮ ዘግቧል። በተመላሽ ስደተኞች ምክንያት መንግስትና የተመላሽ ቤተሰቦች ያገኙት የነበረውን ድጋፍ እንደሚያጡም ጋዜጣው ዘግቧል